# በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት የአፈጻጸም መመሪያ

ጥር 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ 'የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት የአፈጻጸም መመሪያ' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አውጭው አካል

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 10 በተሠጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ማውጫ

ተ.ቁ ርእስ ገጽ

1. መግቢያ ……………………………………………………………………………
2. ትርጓሜ ………………………………………………………………………………
3. ዓላማ ……………………………………………………………………………..
   3.1. ዝርዝር ዓላማ …………………………………………………………………….
4. የሜዲካል ጋዝ አቅርቦትና እና አሰራር ……………………………………………….
   4.1. አደረጃጀት…………………………………………………………………….
   4.2. አሰራር ……………………………………………………………………
   4.3. አቅርቦት …………………………………………………………………
   4.4. የሜዲካል ጋዝ አያያዝ …………………………………………………………
   4.5. የሜዲካል ጋዝ ሲሊኒደር አቀማመጥ ስቶሬጅ ……………………………..
5. ሀላፊነት እና ግዴታዎች ………………………………………………………………..
6. ስልጠና ………………………………………………………………………………
7. ክትትልና ግምገማ ……………………………………………………………
8. መመሪያ መተላለፍ
   8.1. የሜዲካል ጋዝ መመሪያን መተላለፍ ……………………………….
   8.2. የመመሪያ መተላለፍ እርምጃ …………………………………………
9. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ……………………………………………………

## 1. መግቢያ

የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሀገራችን የሚታየውን የበሽታ ክስተትን ልምድ (ትሬንድ) መሠረት ባደረገ መልኩ መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ፖሊሲ ነድፎ ላለፉት 22 ዓመታት የተቀናጀ ርብርብ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል፡፡በእነዚህ ዓመታት የሀገራችንን የጤና ሽፋን ከማሳደግ ጎን ለጎን የጤና አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ እና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ረገድ መንግስት ቆራጥ አመራር በመስጠቱ በሁሉም መስክ ትልቅ ለውጥ ተመዝግቧል፡፡

የጤና ፖሊሲያችንና የተቀረጹ ስትራቴጂዎችን ለማሳካት በሀገራችን ሆስፒታሎች የሚሠጡ አገልግሎት በሁለንተናዊ መልኩ ለማሣደግና ለማሻሻል የለውጥ እርምጃዎች ተጀምረው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከላይ የተመዘገቡት ከፍተኛ ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው በአፈጻጸም ሂደት ውስጥ ከሚታዩ ችግሮች አንዱና ዋነኛው የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት አቅርቦትና አሰራር በቂ አለመሆኑ ሲሆን በተጨማሪ ሆስፒታሎች በራሳቸው አቅም የሜዲካል ጋዝ የማያመርቱ መሆኑ በተደረጉ ግምገማዎች ለመገንዘብ ተችሎዋል፡፡

እነዚህ ምክንያቶች እርካታን ከመቀነሳቸዉም በተጨማሪ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ወደ እነዚህ ጤና ተቋማት በፍላጎት እንዳይሄድ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሜዲካል ጋዝ አቅርቦትና ጥራት መጓደል የሆስፒታሉ ሰራተኞች በሚሰሩበት የጤና ተቋማት ላይ ያላቸው የስራ ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል ፡፡

የሜዲካል ጋዝበህክምና ወቅት እጅግ አስፈላጊ ግብአት መሆኑ ይታወቃል፡፡ለጤና ተቋማቶቻችን በአሁኑ ሰዓት የሜዲካል ጋዝ ከግል አቅራቢ ድርጅቶች ብቻ እየቀረበላቸው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም እስከ አሁን ድረስ የሜዲካል ጋዝ አገልግሎን በሚመለከት ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ የሜዲካል ጋዙን አጠቃቀም እና አያያዝ እንዲሁም አደጋን

መከላከል የሚያስችል ግንዛቤ/ክህሎት እምብዛም የሚታወቅ አሰራር የለም፡፡ የዚህ መመሪያ ዝግጅት የተጠቀሱትንና ሌሎች ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

የጤና ተቋማት የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የአሰራር ሂደት ማሻሻያዎች ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተገባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አንዱ የውስጥ አሰራርን በማሻሻል አገልግሎቶችን በራሱ በተቋሙ /ማስቀጠል ነው፡፡ በሜዲካል ጋዝ ላይ የተዘጋጀው ይህ መመሪያ የጤና ተቋማትን የውስጥ አሰራር ለማሻሻል የሚረዳ ሲሆን በየተቋማቱ ተግባራዊ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት በሆስፒታል/ በተቋማት ውስጥ በተመላላሽም ሆነ ተኝተው ለሚታከሙ ህሙማን እንደአስፈላጊነቱ በባለሙያ ሲታዘዝ የሚቀርብ የግብአት አሰራር ሲሆን ለህክምና አገልግሎቱ ወሳኝ እና ደጋፊ የስራ ሂደት ነው፡፡

ሲሊንደር ውስጥ ያለ የሜዲካል ጋዝ ማለት ለሕክምና አገልግሎት የሚውል በተገቢው መጠን እና ጥራት የቀረበ በሲሊንደር ውስጥ ያለ ኦክስጅን ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ የሜዲካል ጋዝ አጠቃቀም ለማጎልበት እና በአጠቃቀም ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቀነስ ብሎም ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢን በመፍጠር የህክምና አገልግሎቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲቀጥል ማረጋገጥ ነው፡፡

### 3.1. ዝርዝር ዓላማ

- የተገልጋይና የሰራተኞችን እርካታ መጨመር
- የሜዲካል ጋዝ በሆስፒታሎች በራሳቸው የሚመረትበትን ሁኔታ ለማመቻቸት
- ሆስፒታሎች ከራሳቸዉ ፍጆታ በተጨማሪ ሌሎችንም ጤና ተቋማትን መደገፍ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- ድንገተኛ አደጋ እንዳይከሰት ለመከላከል እንዲሁም
- ለሜዲካል ጋዝ ሰራተኞች በስልጠና ለማብቃት ነው፡፡
- በሆስፒታሎች ሜዲካል ጋዝ አገልግሎት በራሱ ወጥ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖረዉ ማስቻል

## 4. የሜዲካል ጋዝ አቅርቦት እና አሰራር

### 4.1. አደረጃጀት

የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ስር ይዋቀራል፣ ኬዝ ቲሙ የስራ ሂደቱ ሃላፊና ሰራተኞች ይኖሩታል፤ በተጨማሪም እያንዳንዱ አገልግሎት በቂ የሆነ የሰው ሃይል ይመደብለታል።

### 4.2. አሰራር

እያንዳንዱ የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት የራሱ ስታፍ ኖሮት የሚመራ ሲሆን በክፍሉ የሚገኙ ባለሙያዎች ተገቢውን ስልጠና ሊያገኙ ይገባል። የሜዲካል ጋዝ አቅርቦት ወይም ግዥ የሆስፒታሉን ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት ክፍሉ አቅርቦቱ እንዲሟላ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

የአቅርቦት እና የአጠቃቀም ሪከርድ ምዝገባ የሚከተሉትን ተግባራትና ሁኔታ ያሟላል።

- ከፍተኛው የሲሊንደር መጠን እና የሜዲካል ጋዝ አይነት
- ከአቅራቢው የተረከበበት ቀን
- ለክፍሎቹ የተሰጠበት ቀን እና የተሰጠው ብዛት በቁጥር
- ለክፍሎቹ የተሰጠበት ቀን እና የተሰጠው ብዛት በአይነት
- የተመረተበት እና አገልግሎት የሚያበቃበት ጊዜ በተመለከተ ሲሆን ይኸም አላስፈላጊ ብክነት ለመቀነስ በበቂ ሁኔታ ሆስፒታሉ የሚያስፈልገው ሲሊንደር መጠን እና አይነት እንዲይዝ ለማስቻል እና የአገልግሎቱን ጥራት ለመጨመር የሚረዳ ነው።

### 4.3. አቅርቦት

4.31.የሜዲካል ጋዝ አቅርቦት ከዚህ በሚከተሉት በአንዱ መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡

- ሕጋዊ ፍቃድ ካለው አካል በግዥ
- ሆስፒታሉ በራሱ በማምረት ሊጠቀም እና ሊያቀርብ ይችላል

4.3.2. የሜዲካል ጋዝ ማምረቻ ቦታዉን በተመለከተ

- ከዋናዉ የህክምና መስጫ ህንጻ ርቀቱ የተጠበቀ ለደህንነት ስጋት በማይሆንበት ቦታ ላይ መገንባት ይኖርበታል

- ከበካይ ጋዝ የጸዳ አካባቢ ላይ እና በቂ የአየር ዝዉዉር ባለበት ቦታ መሆን ይገባዋል
- ከማምረቻዉ እስከ ማሰራጫዉ ቦታ ላይ የሚገኘዉ የማስተላለፊያ መስመሮች ለአደጋ ያልተጋለጡ መሆን ይገባቸዋል

4.3.3 የሚቀርበዉ ሜዲካል ጋዝ የሚከተሉትን ሊያሟላ ይገባል

- የሚቀርበዉ የሜዲካል ጋዝ ጥራቱን የጠበቀ
- የሚቀርበዉ የሜዲካል ጋዝ ትክክለኛዉን መጠን የያዘ መሆን አለበት
- ሲሊንደሩ ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ መሆኑ መረጋገጥ አለበት
- ሲሊንደሩ ከሞሞላቱ በፊት በሚገባ ዉስጣዊ ክፍሉ መጽዳት አለበት
- የሜዲካል ጋዙ በትክክልኛዉ የመለያ ቀለም በያዘ ሲሊንደር እንዲሁም መስመር መጠቀም ይገባዋል፡፡

## 4.4. የሜዲካል ጋዝ አያያዝ

- ሁሉም የሜዲካል ጋዝ ሰራተኞች ስለ ሜዲካል ጋዝ አያያዝ ስልጠና የወሰዱ መሆን አለባቸዉ ፡፡
- ሲሊንደሩን የሚያጋግዙ ሰራተኞች ከማጓጓዝ በፊት ስለሚፈጠርሩ ድንገተኛ አደጋዎች እና መወሰድ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ ማወቅ አለባቸው፣
- የሲሊንደር አጠቃቀም /ቅድመ እና ድህረ / የውስጥ አሰራር ፕሮቶኮል እንዲኖረው ያስፈልጋል ፣
- ሲሊንደሩን ከመጠቀም በፊት በተገቢው የሲሊንደር አጠቃቀም ፕሮቶኮል መሰረት መሆኑ ማረጋገጥ ይገባል፣
- በምንም ሁኔታ ሲሊንደሩ በሃይል ሊመታ አይገባም በተጨማሪም እንዳይወድቅ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል
- ሲሊንደሩን በምንም ሁኔታ በዘይትም ሆነ በሌላ ቅባት ሊነካው አይገባም፣ በእጅ ላይ ቅባት አድርጎ ከስሊንደሩ ጫፍ ጋር ማነካካት የተከለከለ ነው፣
- የሲሊደሩን ውስጣዊ እና ውጫዊ አካል ንጽህናው በሚገባ የተጠበቀ መሆን አለበት

- የአረጁ እና ደህንነታቸዉ ያልተጠበቀ ሲሊንደሮችን ግዜያቸዉን ጠብቀዉ እንዲቀየሩ ማድረግ፡፡
- ሲሊንደሩን ለራሱ አገልግሎት ተብሎ በተዘጋጀዉ ጋሪ መጓጓዝ ይገባዋል፡፡በምንም ዓይነት ሁኔታ ብቻዉን እየጎተቱ ወይም እያንከባለሉ ማጓጓዝ የተከለከለ ነዉ፡፡
- ሲሊንደሩ ላይ የሚገጠመዉ ጌጅ ፣ ፍሎዉ ሜትር እና አናላይዘር በየግዜዉ በትክክል ስለመስራታቸዉ ፍተሻ መደረግ አለበት፡፡

### 4.5 የሜዲካል ጋዝ ሲሊንደር አቀማመጥ/ ስቶሬጅ

- አገልግሎቱን በአግባቡ የሚከታተል ባለሙያ ይመደባል፣
- የሜዲካል ጋዝ ከሌሎች ቁሳቁሶች በመለየት ለብቻው እንዲቀመጥ ይደረጋል ፣
- ሙቀት አምጭ በሆኑ አካባቢዎች ሲሊንደር አይቀመጥም: በማስቀመጫው አካባቢ እንዳይጨስ እና የሚቀጣጠሉ ነገሮች እንዳይመቀመጡ ማስጠንቀቂያ ይለጠፋል፣
- ክፍሉ በቂ ስፋት ኖሮት ሲሊንደሮችን በቀላሉ ለመለየት በሚያስችል አቀማመጥ ሊዘጋጅ ይገባል
- ሲሊንደሮች መቀመጥ ያለባቸው እርጥበት በሌለበት ንጹህ እና ደህንነቱ በሚጠበቅ ክፍል ውስጥ ሲሆን ለከፍተኛ ሙቀትም ሆነ ለቅዝቃዜ መጋለጥ የለበትም፣
- ሲሊንደሮች ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ለራሱ ተብሎ የተሰራ ጋሪ ሊኖረው ይገባል፡፡ እንዲሁም ክሊኒክ አካባቢ ዋርድ ወይም ክፍል በሚቀመጥበት ጊዜ ተገቢው ጥንቃቂ ሊደረግ ይገባል በተጨማሪም በሮችም ሆነ የእሳት አደጋ መውጫዎችን ዘግተው መቀመጥ የለባቸውም፣
- ድንገተኛ አደጋ በሚፈጠር ጊዜ ሲሊንደሮች እሳት አደጋ እንዳያደርሱ ለእሳት አደጋ ሰራተኞች ሲሊንደሩ የሚገኝበትን ቦታ የሚያውቁበት መንገድ ይመቻቻል፣

## 5. ሀላፊነት እና ግዴታዎች

ሆስፒታሉ/የጤና ተቋማት/ የሚከተሉትን ሊያማላ ይገባል

- ለአገልግሎት የተለየ ክፍል ያዘጋጃል፣
- በቂ የስራ ማስኬጃ በጀት መያዙን ያረጋግጣል፣
- ባለሙያዎች መመደባቸውን ያረጋግጣል፣
- በሆስፒታሉ የሜዲካል ጋዝ እንዲመረት ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- ይህ መመሪያ ለሁሉም ሜዲካል ጋዝ ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

- የሜዲካል ጋዝን አስመልክቶ ቅደመ አደጋ መከላከል ጥናት መደረጉን ያረጋግጣል፣
- ተገቢው መሳሪያ እንዲሁም ሲሊንደር በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ያረጋግጣል
- የሜዲካል ጋዝ ባለሙያዎች ተገቢውን ስልጠና ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣

## የሜዲካል ጋዝ ሰራተኞችን በተመለከተ

- ከአቅራቢ አካል ሲሊንደሩ በበቂ መጠንና ጥራት መቅረቡን አረጋግጦ ይረከባል፣
- ለአገልግሎት ዝግጁ የሆኑትን ሲሊንደሮች በወቅቱ ያቀርባል ለየክፍሉ ባለሙያ በመረካከቢያ ቅጽ ያስረክባል፣
- የሜዲካል ጋዝ አመራረት ላይ የስራ ድርሻውን ይወጣል፣
- መረጃዎችን ትእዛዞችን እና በስልጠና ያገኘውን ክህሎት ተግባራዊ ያደርጋል፣
- መሳሪያዎችን በጥንቃቄ እና በአግባቡ ይይዛል፣
- በመሳሪያዎች አጠቃቀም ደህንነት ላይ መሪ ተዋናይ ይሆናል፣
- የሚያጋጥሙ ድንገተኛ ሆነ ሌሎች ችግሮችን ለበላይ አካል ሪፖርት ያቀርባል፣
- ከክፍሉ ጋር ቅድመ አደጋ መከላከል ጥናት ያደርጋል ግኝቱም ለበላይ አካል ሪፖርት ያቀርባል፡፡
- ማንኛውም የሜዲካል ጋዝ ላይ የሚሰራ ሰራተኛ ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፣

- የሜዲካል ጋዝ ክፍሉ አመታዊ እቅድ ለበላይ አካል  ያቀርባል፡፡

## ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል

- የአገልግሎት መመሪያ ይቀርባል፣
- የተዘጋጀው መመሪያ ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል
- እንደአስፈላጊነቱ በሜዲካል ጋዝ አጠቃቀም ዙሪያ አገልግሎቱ እንዲዳብር ቀጣይ የሆነ የማሻሻያ ስራ ይሰራል፣
- ለባለሙያዎች ስልጠና እንዲሰጥ ያመቻቻል፣
- የሜዲካል ጋዝ በሆስፒታሎች እንዲመረት ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 6. ስልጠና

የሜዲካል ጋዝ አሰራር ለማሻሻል አቅርቦቱ ሳይቋራረጥ በመቀጠል የአገልግሎቱ ጥራት እየተሻሻለ እንዲሄድ ለማስቻል ለባለሙያዎች የስራ ላይ ስልጠና መስጠት እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም የሜዲካል ጋዝ ሰራተኞች የሚከተሉትን ስልጠና ሊወስዱ ይገባል፡፡ ይህ ስልጠና በአመት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ለባለሙያ የሚሰጥ ሲሆን የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፡፡

- የሜዲካል ጋዝ ምንነት እና ባህሪያቸውን የክሊኒካል ጥቅም፣
- የሜዲካል ጋዝ ሲሊንደር መለየት አቀማመጥ እና አያያዝ
- ስለተበላሹ ሲሊንደሮች አወጋገድ/አያያዝ፣
- ሜዲካል ጋዝ እና ድንገተኛ አደጋ እንደ እሳት/ፍንዳታ መከላከል
- የሜዲካል ጋዝ አመራረት

## 7. ክትትልና ግምገማ

የክትትልና ግምገማ ግልፅ በሆነ አሠራር ላይ የተመሠረተ ሆኖ እንደ ሌሎች የስራ ክፍሎች ሁሉ በታካሚው እንቅስቃሴና በተቋሙ አሠራር ላይ ትኩረት የሚያደርግ እና የሚሰጠው የሜዲካል ጋዝና ተያያዥ አገልግሎትም በተገቢው ደረጃና ጥራት ላይ መሆኑን አጥብቆ የሚከታተል ይሆናል።

ለግምገማ እና ክትትሉ የሚያስፈልጉ አመላካች የሚሆኑ ጠቋሚ አመልካቾች ይኖረዋል። አመላካቾቹ የተለያዩ የአንድን ስራ ሂደትን የሚያሳዩ ደረጃዎች ማለትም ግብዓት፤ ክንዋኔ፤ ውጤት እና ስኬት የሚያሳዩ እንዲሆን ይጠበቅባቸዋል።

የሜዲካል ጋዝ አገልግሎት ቡድን መሪ በስሩ ከሚገኙ የክፍሉ ሰራተኞች በተዋቀረ መደበኛ በሆነ አካሄድ የስራ ክፍሉን ስራዎችና አፈፃፀሞችን ይከታተላል።

ለክትትል እንዲረዳው ቼክ ሊስት በመቅረፅ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምዘናን ያካሄዳል፣ የምዘናውንም ሪፖርት ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል። በተገኘው ውጤት መሰረትም በሰራተኛው መካከል የውድድር መንፈስ በመፍጠር የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡትን ይሸልማል፤ ያበረታታል።

በየዕለቱ ሠራተኞች እንደ ቡድን ሥራ የሚሠሩበት ሥራዎቻቸውንና ያጋጠማቸውን ችግር በዝርዝር የሚያሰፍሩበት መዝገብ እንዲኖር ያደርጋል። መዝገቡ የክፍሉ ባለሙያዎች

በየሣምንቱ በሚያደርጉት ስብሰባ ሥራቸውን በጥልቀት የሚፈትሽና የሚቀርብ አስተያየት ወይም ውሣኔ ይመዘገብበታል፡፡

- በተገልጋዩ ህብረተሰብ ስለተቋሙ ሀሣቡን በነፃነት ከሚገልፅበት የሀሣብ መስጫ ሣጥን ውስጥ በሜዲካል ጋዝ ላይ የተሰጡትን ጥቆማዎች እና አስተያየቶችን በመለየትና በመገምገም መፍትሄ የሚፈለግበት መንገድ መቻቻል፤
- የክፍሉ አስተባባሪ መጠይቆችን ለተገልጋዩ ወይም ለአገልግሎት ሰጭው እንደአስፈላጊነቱ በማቅረብ ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን ያረጋግጣል፣ የሚያገኘውንም መረጃ ለሚመለከተው ክፍል እያቀረበ ያስወስናል፣
- የክፍሉ አስተባባሪ በየጊዜው ክትትል በማድረግ ግልፅነትና ተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ አሠራር እንዲሰፍን የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

በተጨማሪም የክፍሉ ሀላፊው የሜዲካል ጋዝ ፍላጎት እና አቅርቦቱን እንዲሁም ቆጠራ እና ቁጥጥር የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡

ሆስፒታሉ በቂ የሆነ የሜዲካል ጋዝ ሲሊኒደር ሊኖረው ይገባል ይህም አገልግሎቱን ሳይቋረጥ እንዲቀርብ እንዲያስችል ነው፡፡ ይህንኑ እንዲያግዝ የሜዲካል ጋዝ ክፍሉ አመታዊ እቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡

## 8. መመሪያ መተላለፍ

### 8.1. የሜዲካል ጋዝ መመሪያን መተላለፍ

ማለት አገልግሎት ሰጭ ባለሙያ/ሠራተኛ በእንዝላልነት ወይንም ሆን ብለዉ የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ወይንም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሆነ ብለው የዚህን መመሪያ አሰራር መጣስ ወይንም ደንቡን ከሚጥሱት ጋር መተባበር ማለት ነዉ፡፡

ይህም ሲባል፡-

- የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብና በክራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ዉስጥ በመዘፈቅ የዲሲፕሊን ግድፈትን መፈፀም፤
- በክፍሉ በተቀመጠዉ የሥራ ሰዓት በሥራዉ ላይ ያልተገባ ሥነ ምግባር ማሳየት ወይንም መፈፀም፤

## 8.2. የመመሪያ መተላለፍ እርምጃ

ማንኛዉም ባለሙያ/ሠራተኛ የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ መመሪያ ሲጥስ ወይንም ከሚጥሱት ጋር ሲተባበር፤ በመንግስት ሠራተኛ መተዳደርያ ደንብ መሠረት ኃላፊነት በተሰጠዉ ህጋዊ የመንግስት አካል የሚወሰድ እርምጃ ማለት ነዉ፡፡

# 9. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

- ማንኛውም የመንግስት ሆስፒታል ይህንን መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት።
- ይህ መመሪያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማሻሻል ያስፈልጋል ብሎ ባመነበት በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል።
- ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፀደቀ ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
ጥር 2011 ዓ.ም.